በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. 00.9.ሺ.6/1/7
ቀን
Date 0 2 ህዳር 2012

በዝርዝሩ ለተመለከቱት በሙሉ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመግአ የአሰራር ማኑዋል ፀድቆ ሥራ ላይ መዋሉን ስለማሣወቅ</u>

የሀገራችንን የተፋጠነ ኢኮኖሚ ዕድገት ለማስቀጠልና የግል ዘርፉ በልማት ሂደቱ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ እንዲሁም እያደገ የሚሄደውን የህዝብ የልማት ፍላጐትና የሕዝብ አገልግሎትና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በመንግሥት ፋይናንስ ብቻ መሸፈን ስለማይቻል የግል ባለሀብቱ ከመንግሥት ጋር በአጋርነት የሚሠራበት አሠራር የመንግሥትና ግል አጋርነት (መግአ) አንደ አንድ ስትራቴጂ በመንግሥት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ተገቢው ፖሊሲ፣ አዋጅና መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ መገባቱ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት በመ/ቤታችን የመግአና የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ዘርፍ በሚኒስትር ዴኤታ ደረጃ ተደራጅቶ ቴክኒካዊ ሥራው ሙሉ በሙሉ በመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ደረጃ የሚመራ ሲሆን በመግአ አዋጅ ቁጥር 1076/2010 አንቀጽ 8/1 መሠረት በተቋቋመ የመግአ ቦርድ የሚመራ ነው፡፡ ለመግአ ትግበራ አስፈላጊ ፖሊሲ ህግና መመሪያ ተቀርጾ ትግበራው የተጀመረ ቢሆንም ከሥራው ጥልቀትና ዓለም አቀፋዊ ይዘት አኳያ ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የመግአ የአሰራር ማኑዋል /Generic and Sector based Guideline/ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ በመ/ቤታችን አስተባባሪነት እና በዓለም ባንክ የፋይናንስ ድጋፍ የዓለም አቀፍ አማካሪዎች ከመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ባለሞያዎች ጋር በመተባበር ረቂቅ ማንዋል ተዘጋጅቶ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተወያይተውበት አስፈላጊውን ግብዓት እንዲሰጡበት ከተደረገ በኋላ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የሰነዱን ኮፒ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሲዲ የላክን መሆኑን እየገለጽን ከዛሬ ሕዳር 1/2012 ዓ.ም ጀምሮ ማናቸውንም የመግአ መዓቀፍ አፈፃፀም የምናስተናግደውና የምንመራው በዚህ የአሠራር ማንዋል መሠረት መሆኑን አስታወቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

<u>ግልባጭ</u> ፣

- ለክቡር የኢኮኖሚ ትብብር ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ
- ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ
- ለክቡር የመግአና የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ዘርፍ ሚ/ር ዴኤታ
- ለክቡር አቶ ኢብራሂም ኡስማን በሚ/ር ዴኤታ ማዕረግ የክቡር ሚ/ር አማካሪ
- ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
- ለመግአ ቦርድ ጽ/ቤት

<u>ገንዘብ ሚ/ር</u>

ስልክ
Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

ለሰላም ሚኒስቴር
ለግብርና ሚኒስቴር
ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
ለትራንስፖርት ሚኒስቴር
ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
ለውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር
ለትምህርት ሚኒስቴር
ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
ለጤና ሚኒስቴር
ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
ለፕላንና ልማት ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
ለአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል
ለኢትዮጵያ ኤሌትሪክ አገልግሎት
ለኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኤጀንሲ
የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን
ለኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን
ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች አስተዳደርና ባለይዞታ ኤጀንሲ

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
5